
DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2021-2022



# የወላጅ የማወቅ-መብት መመሪያ

**አድልዎ-ያለማድረግ እና በቀል-ያለማድረስ ማሳወቂያ።**

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ሁሉም ሠራተኞች ለፌደራል እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት አድልዎ-ያለማድረግ (non-discrimination) ህጎች ተገዢ ሆነው ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆናቸውን፣ ወላጆች የማወቅ መብት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በትጋት ይሰራል። አድልዎ፣ ጥቃትን፣ ወይም በቀልን አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት፤ እባክዎትን በኢሜይል አድራሻ dcps.grievance@dc.gov ወይም OCR@ed.gov ያነጋግሩ። ለአካል ጉዳተኞች አሜሪካውያን ድንጋጌ (ADA) የሰራተኛ አስተዳደርና የሰራተኛ ግንኙነት ጽ/ቤት (LMER)፤ በስልክ ቁጥር (202) 442-5424 መገኘት ይችላል።

**አስተማሪዎች እና ባለሙያዎች (Paraprofessionals)።**

ሁሉም አስተማሪዎች እና ባለሙያዎች ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት - የስቴቱን የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education) ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ለማግኘት ተፈጻሚነት ያላቸውን መስፈርቶችን ማማሏት እንዳለባቸው፤ የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን ድንጋጌ (Every Student Succeeds Act (ESSA) ይደነግጋል። በተጨማሪም፣ ESSA ወላጆች የልጃቸውን የክፍል-ውስጥ አስተማሪዎች ሙያዊ ብቃቶች በተመለከተ መረጃ የመጠየቅ መብት ይሰጣቸዋል። በተጠየቀ ጊዜም፣ DCPS ይህንን መረጃ ለወላጆች በወቅቱ ማቅረብ አለበት።

**የተማሪ ስኬታማነት (PARCC ዳታ)።**

የ'PARCC' ውጤቶችን፣ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ድህረ-ገጽ ላይ፣ ወላጆች በማግኘት - የማወቅ-የሚችሉበት መብት አላቸው።

**የተማሪ መዛግብት (Records)።**

DCPS ለወላጆች እና ለአዋቂ ተማሪዎች በFERPA ስር ስላለው መብታቸው ማሳወቅ አለበት፣ DCPS ይህንን የሚያደርገው ሰነዶቹን በምዝገባ ጥራዝ (enrollment packet) ውስጥ በየዓመቱ አያይዞ በማቅረብ ነው።

**ደህንነቱ-ያልተጠበቀ ትምህርት ቤት ምርጫ ላይ ያሉ አማራጮች።**

በትምህርት ቤት ውስጥ ልጅዎ የአመጻዊ-ወንጀል ውስጥ ተጠቂ-መሆኑን፤ የማወቅ መብት አለዎት። በተጨማሪም፣ ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ የአመጽ ወንጀል ተጠቂ ከሆነ፣ ልጅዎ ዝውውር-እንዲያገኝ የመጠየቅ መብት አለዎት። ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የሃቀኝነት ጽ/ቤት (Office of Integrity)ን፣ በስልክ ቁጥር (202) 939-4913 ያነጋግሩ።

**እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚማሩ (ELs)።**

ወላጆች የሚከተሉትን የማወቅ መብት አላቸው፥ 1) ስለልጃቸው የእንግሊዝኛ የብቃት ደረጃ (PL)፣ 2) DCPS የሚለኩ ዓመታዊ ግቦቹን ማሳካት ወይም አለማሳካቱን፣ እና 3) በልጃቸው ትምህርት ላይ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ። ለተጨማሪ መረጃ፤ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) ውስጥ የመማር ማስተማር ቢሮን፣ በስልክ ቁጥር (202) 671-0750 ያነጋግሩ።

**ለመኖሪያ ቤት-አልባ ልጆች፣ የትምህርት መብቶች ማሳወቂያ።**

ወላጆች ለመኖሪያ ቤት አልባ ልጆች ትምህርት ቤት የመምረጥ እና ተመሳሳይ የሆነ አገልግሎቶችን – መጓጓዣ፣ ትምህርታዊ አገልግሎቶች፣ እና ምግብ የማግኘት መብት አላቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ የትምህርት ቤት ማሻሻያዎች እና እርዳታዎች ቢሮን፣ በስልክ ቁጥር (202) 576-9502 ያነጋግሩ።

**የ'Title I' ፕሮግራሞች።**

ትኩረት ስለተደረገባቸው የድጋፍ እና ትምህርት ቤት አቀፍ የ'Title I' ፕሮግራሞች ላይ፣ መረጃ የማግኘት መብት አለዎት። እባክዎን የ'Title I' ትምህርት ቤቶች ሙሉ ዝርዝርን እዚህ ይመልከቱ። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን የመቆጣጠሪያ እና ፕሮግራም እገዛ ቡድን (Monitoring and Program Support team)ን በስልክ ቁጥር (202) 442-6025 ያነጋግሩ።

**የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ።**

ወደተሻሻለ የተማሪዎች የቀለም-ትምህርት ውጤታማነት፤ ትምህርት ቤቶችን፣ የትምህርት ቤት-የወላጅ ስምምነቶች (የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ) በመቅረጽ ላይ፣ ወላጆች የመሳተፍ መብት አላቸው።። ለተጨማሪ መረጃ፣ የግንኙነቶች (Communications) እና ተሣትፎን በ(202) 719-6613 ያነጋግሩ።

**አቤቱታን መፍታት።**

ወላጆች ያቀረቡትን አቤቱታ በ60 የስራ-ቀናት ውስጥ እንዲፈታ የሚያስችል መብት አላቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ የሃቀኝነት ጽ/ቤትን (Office of Integrity)ን በ(202) 939-4913 ያነጋግሩ። ወላጆች፤ የስቴቱን የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) ሊያነጋግሩ የሚችሉ እና ህጋዊ አቤቱታን ፋይል ማድረግም ይችላሉ። ለ'OSSE ' አቤቱታ-የማቅረቡ ሂደቶች፣ እዚህ መገኘት የሚችል ሲሆን፤ ወይም በ(202) 741-6404 በማነጋገር ማግኘት ይቻላል።